## የሴት ልጅ ግርዛት (FGM/C) እውነታዎች

**የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛት (FGM/C) የማስቆም ቁርጠኛ አቋም አለው። ለግርዛት አደጋ የተጋለጡ ከሆነ፣ ለግርዛት አደጋ የተጋለጠች ሴት የሚያውቁ ከሆነ፣ ወይም ለግርዛት ስለ ተዳረጉ መረጃ የሚፈልጉ ከሆነ፣ እባክዎ ከታች በተጠቀሰው ቁጥር ይደውሉ።**

## የሴት ልጅ ግርዛት (FGM/C) ምንድን ነው?

የሴት ልጅ ግርዛት (FGM/C) በሕክምና ባልተደገፈ ምክንያት የሴት ልጅን ብልት መቁረጥ ወይም የሴት ልጅ ብልትን የሚጎዱ ሌሎች ድርጊቶችን ያመለከታል። በተወሰኑ የዓለማችን ክፍሎች 'የሴት ልጅ ግርዛት' በመባል ይታወቃል። ድርጊቱ ምንም ዓይነት የጤና/የሕክምና ጠቀሜታ የሌለው ከመሆኑም በላይ ለበርካታ የአካል እና የአይምሮ ችግሮችን ሊዳርግ ይችላል።

## የሴት ልጅ ግርዛት (FGM/C) በጤና ላይ የሚያደርሱት ጉዳቶች ምንድን ናቸው?

በቀጥታ የሚደርሷቸው ጉዳቶች የደም መፍሰስ፣ ከባድ የህመም ስሜት እና አንዳንድ ጊዜም ሞት ሊያስከትሉ ይችላሉ። ዘላቂ የሆኑ የጤና ችግሮች የሽንት ስርዓት በሽታዎች፣ ፊስቱላ፣ መካንነት፣ በወር አባባ ወይም በግብረ-ስጋ ግኑኝነት ግዜ ከባድ የህመም ስሜት፣ እንዲሁም ለኤችቪ/ኤይድስ በሽታ የመጋለጥ አደጋ መጨመርን ያካትታሉ። በተጨማሪም የተገረዙ ሴቶች ካልተገረዙ ይልቅ በወሊድ ጊዜ ለሚፈጠሩ ችግሮች የበለጠ የመጋለጥ እድል ያጋጥማቸዋል እንዲሁም በግርዛት ምክንያት የሞሞት እድላቸው ካልተገረዙት ይልቅ የበለጠ ነው። በመጨረሻም ድርጊቱ አብዛኛውን ግዜ ልጃገረዶች እና ሴቶች የፍራቻ ስሜት፣ የስነ-አይምሮ ጠባሳ፣ የሃፍረት ስሜት እና ጭንቀት እንዲኖራቸው ያደርጋል።

## የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት በሴት ልጅ ግርዛት ላይ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?

***የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት በማንኛውም ዓይነት፣ ደረጃ፣ ወይም ክብደት የሚፈጸም የሴት ልጅ ግርዛትን፣ እንዲሁም ለድርጊቱ መፈጸም የሚሰጠው ምክንያት የፈለገ ቢሆንም ይቃወማል።*** የሴት ልጅ ግርዛት በባህላዊ እምነቶች እና የጉርምስና ጊዜ ባህላዊ ስነ-ስርዓት ምክንያት ሊፈጸም እንደሚችል የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት ይገነዘባል። ሆኖም ግን፣ የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛትን እንደ ከባድ የሰብ አዊ መብት ጥሰት እና ጾታ-ነክ እና የህጻናት ጥቃት አድርጎ ይመለከተዋል።

## የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት ይህንን የሴት ልጅ ግርዛት የሚመለከት ማሳሰቢያ  የሰጠበት ምክንያት ምንድን ነው?

የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም ቁርጠኛ አቋም የወሰደበት ምክንያት በአለም ደረጃ የልጃገረዶች እና የሴቶች ጤንነት እና ደህንነት ለማስጠበቅ እና መብቶቻቸውን ለማረጋገጥ ነው። የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት የሴት ልጅ ግርዛት በልጃገረዶች እና ሴቶች ላይ የሚያስከትሉትን ከባድ እና ጎጂ የሆኑ ውጤቶችን በተመለከተ ህዝብን ለማስተማር በውስጥም ሆነ በሌሎች ሀገራት ላይ እየሰራ ይገኛል።

## የሴት ልጅ ግርዛት መፈጸም ወይም የድርጊቱ ተባባሪ መሆን የሚያስከትላቸው ሕጋዊ ውጤቶች ?

ከ18 አመት በታች በሆነች ሴት ልጅ ላይ ግርዛት መፈጸም፣ ወይም ለማስገረዝ ወደ ሌላ አገር መላክ ወይም ለመላክ መሞከር የአሜሪካን ሕግ የሚጻረር ነው። ሕጉን መጣስ እስከ 5 አመት የሚደርስ እስራት፣ የገንዘብ መቀጮ፣ ወይንም ሁለቱንም ያጣመረ ቅጣት ያስከትላል። ልማድን ወይም ባህልን ምክንያት በማድረግ የሚደረግ የሴት ልጅ ግርዛት ይቅርታ አይደረግለትም። ከ18 አመት በታች የሆነች ሴት ልጅ ብልት ላይ ጉዳት የሚያስከትል መቁረጥ እና ሌሎች ድርጊቶች መፈጸም በዩናይትድ ስቴትስ ሕግ የተከለከለ ነው።

## የሴት ልጅ ግርዛትን የሚከለካሉ ሕግጋት መጣስ በስደት ሁኔታዎ ላይ የሚያስከትሏቸው ውጤቶች ምንድን ናቸው?

የሴት ልጅ ግርዛትን የሚከላከሉ ሕግጋት (ያለ ወንጀል ችሎት) ወደ ዩናይትድ ስቴትስ እንዳይገቡ መከልከል ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ መባረር እና አንዳንድ የስደተኛ ጥቅማ-ጥቅሞች ለመጠቀም ብቁ አለመሆንን ያካተቱ የስደት ሁኔታዎን የሚነኩ አሉታዊ ውጤቶች ሊያስከትሉ ይችላሉ።

## ግርዛት የተደረገላቸው ሴቶች የጣሷቸው ማንኛውም ሕጎች አሉን?

***ግርዛት የተፈጸመባት ልጃገረድ ወይም ሴት ምንም ጥፋት የለባትም። የግርዛት ድርጊት ስለተፈጸመባት የጣሰችው ማንኛውም ሕግ የለም።*** አንዲት ሴት ግርዛት ስለተፈጸመባት/ስለተገረዘች ወደ ዩናይትድ ስቴትስ የመጓዝ ወይም የስደተኛ ጥቅማ-ጥቅሞች የማግኘት ብቁነቷ ላይ አሉታዊ ውጤት አይኖረውም።

## ተጨማሪ መረጃዎች ከየት ማግኘት ይቻላል?

ለግርዛት አደጋ ከተጋለጡ ወይም ግርዛት ከተፈጸሙብዎት፣ ወይም የሴት ልጅ ግርዛትን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ካልዎት፣ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሴት ልጅ ግርዛት የሚፈጽም ሰው የሚያውቁ ከሆነ፣ ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ወይም ከዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ለግርዛት አደጋ የተጋለጠች ሰው የሚያውቁ ከሆነ፣ ማግኘት ስሊሚችሏቸው እርዳታዎች ወይም መረጃዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ በ **1-800-994-9662** ይደውሉ።